## የእግዚአብሔርን መንግሥት በመጸሀፈ ነህምያ
## የእግዚአብሔርን መንግሥት ተሃድሶ፣ በድፍረትና በታዛዥነት መገንባት

**ምንባብ፡-** ነህምያ 1:1–11፤ 2:17–20፤ 4:14, 17–18፤ 6:15–16፤ 8:1–12፤ 9:1–3, 33

**መግቢያ**

የነህምያ መጽሐፍ ከቅጥር ግንባታ ፕሮጀክት ያለፈ ትርጉም አለው። እርሱም የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ ነው። የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ፈርሰው፣ ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ፣ ከተማዪቱም በ ውርደት ውስጥ ነበረች፤ይሁን
እንጂ እግዚአብሔር ከኪዳኑ ሕዝብ ጋር ያለው ታሪክ ግን አላበቃም ነበር።በዚህ ምክንያት የፈረሰውን እንዲገነባ፣ የተተወውን እንዲያድስ፣ እና የጠፋውን መልሶ እንዲያቋቁም ነህምያን አስነሳው።በዚህ
ትምህርት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ስንናገር፣ **ስለ እግዚአብሔር ገዥነት፣ ስለ ሥልጣኑ** እ ና **በሕዝቡ መካከል ስላለው ሥራ** እየተናገርን ነው። በነህምያ መጽሐፍ ውስጥ፣ መንግሥቱ የ ሚታየው የነገሥታት ዙፋን ባለበት አዳራሽ ውስጥ ሳይሆን **በጸሎት ክፍል፣ በከተማ ቅጥሮች፣ በቃሉ ሕዝባዊ ንባብ፣ በንስሐ** እና **በታማኝ አገልግሎት ውስጥ ነው።**የነህምያ
መጸሀፍ መልእክቱ ግልጽ ነው እግዚአብሔር በሚገዛበት ቦታ ሁሉ፣ **መታደስና መመለስ** ይከ ተላል የሚል ነው።

### 1. የመንግሥቱ ተሀድሶ የሚጀምረው ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ሸክም ነው (ነህ 1:5–11)

የነህምያ መጸሀፍ ታሪክ የሚጀምረው ኢየሩሳሌም በችግር ውስጥ መሆኗንና ቅጥሮቿም መፍረ ሳቸውን በሰማ ጊዜ ነህምያ የሰጠውን ምላሽ በመዘገብ ነው።የነህምያ የመጀመሪያ ምላሽ ማጉረምረም፣ መሸሽ ወይም ሌሎችን መውቀስ አ ልነበረም።ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት **ተቀመጠ፣ አለቀሰ፣ ጾመ፣ ጸለየም።**ምክንያቱ የመንግሥቱ ሥራ የሚጀምረው እግዚአብሔ ር በልባችን ላይ በዚህ ሂደት ውስጥ በሚያስቀምጠው ሸክም ነው ።በምዕራፍ 1 ላይ ያለው የነህምያ ጸሎት በአክብሮት፣ በ ኑዛዜ እና በኪዳን እምነት የተሞላ ነው። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ያውጃል፣ የተስፋ ቃሉንም ያስባል። ሕዝቡ ንጹሕ እንደሆኑ አያስመስልም፤ የራሱንና የአባቱን ቤት ኃጢአት ጨምሮ የእ ስራኤልን ኃጢአት ይናዘዛል። ይህ ለመንግስቱ
ተህድሶ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት በኩራት ላይ አይገነባ ም። የሚገነባው በእግዚአብሔር ፊት በሚሆን ትሕትና ላይ ብቻ ነው። **ከእግዚአብሔር ዘንድ ሸክም ያለው ሰው ስብራትን የሚያየው በተለየ መንገድ ነው።** ሌሎች ፍርስራሹንና ተስፋ መ ቁረጥን ብቻ ሲያዩ፣ የመንግሥቱ ሰዎች ግን ፍርስራሹን አይተው፣ “እግዚአብሔር እንድንገነባ ው እየጠራን ያለው ምንድን ነው?” ብለው ይጠይቃሉ።

**ተግባራዊ ተዛምዶ፡-** እግዚአብሔር በልባችን ላይ ሸክም ካኖረ፣ ቸል አንበል።ምናልባት እግዚአብሔር የመንግሥቱን ሥራ በሕይወታችን ውስጥና በሕይወታችን በኩል መስራርት የሚጀምርበት ሊሆን ይችላል።

**2. የመንግሥቱ ተሀድሶ በእምነት ላይ የተመሠረተ ራዕይ ያስፈልገዋል** (ነህምያ 2:17-20)

ነህምያ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣ የቅጥሩንና የከተማውን የመውደም እውነታ ከህዝቡ አልደበቀም። ቅጥሮቹን በጥንቃቄ ተመለከተ፣ ከዚያም ለሕዝቡ የ ማበርታቻ ቃል እንዲህ ሲል ተናገራቸው:- **"ኑ፣ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ።** "ነገር ግን ሥራው በቀላል የሚከናወን እንደሚሆን ቃል አልገባላቸውም። ነገር ግን በእርሱ ላይ ወዳ ለችው የእግዚአብሔር እጅ አመለከታችው ወይም **"ስለ መልካሚቱ የአምላኩ እጅ" ነገራቸው።**ነህምያ ያደርገው የእግዚአብሔር መንግሥት ራዕይ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ እውነት ነው።ነህምያ ያደርገው ችግሩን መካድ አይደለም፣ነገር ግን በሰው ኃይል ላይ አለመታመንን ማረጋገጥ እና በሰማይ አምላክ ላይ መታመንን ማጽናት ነው። ነህምያ እግዚአብሔር ሰለጠራቸው፣ እግዚአብሔር ደግሞ እንደሚደግፋቸው አመነ።በዚህ ጊዜ ጠላት በፍጥነት በፌዝና በዛቻ መጣ። ሰንባላጥና ጦብያ ግንበኞቹን በማሸማቀቅ ስራውን ለማስቀም እየሞከሩ ሥራውን አናናቁ። **ነህምያ ግን በመፍራት ሳይሆን በእምነት መለ ሰላቸው።** የእግዚአብሔር መንግሥት በስድብ ወይም በማስፈራራት ሊፈርስ እንደማይችል ያ ውቅ ነበርና።

**ተግባራዊ ተዛምዶ፡-** አማኞች ሁኔታዎችን በሰው ደካማነት መለካት አቁመው በእግዚአብሔር ታማኝነት መለካት ሲጀምሩ የመንግሥቱ ተሀድሶ ወደ ፊት ይገሰግሳል።

**3. የመንግሥቱ ተሀድሶ በግልሰብ ሳይሆን በብዙ እጆች ይገነባል** (ነህምያ 3:28)

የነህምያ መጽሐፍ ምዕራፍ 3 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት እጅግ ውብ የእግዚአብሔር መ ንግሥት ትብብር ከሚያያሳዩ ሥዕሎች አንዱ ነው። ካህናት፣ ገዢዎች፣ ቤተሰቦች፣ አንጥረኞች ፣ ነጋዴዎችና ተራ ሠራተኞች ሁሉ ለቅጥሩ መታደስ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። አንዳንዶቹ በሮ ቹን ጠገኑ፣ አንዳንዶቹ ቅጥሩን አደሱ፣ አንዳንዶቹ በገዛ ቤታቸው አጠገብ ያለውን የቅጥሩን ስራ ሠሩ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለረጅም ክፍሎች ኃላፊነት ወሰደው ሰሩ።ይህ ምዕራፍ የሚያስተምረን የእግዚአብሔር መንግሥት **በአንድ ታዋቂ መሪ ብቻ** እንደ ማይገነባ ነው።ነገር ግን የሚገነባው እያንዳንዳቸው ድርሻቸውን በሚወጡና አንድነታቸው በተጠበቀ ሕዝቦች ነው ።በህብረት

ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ዋጋ አለው። እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል ዋጋ አለው። እያንዳንዱ የ ታማኝነት ተግባር ትርጉም አለው። ሕዝቡ ሁሉ አንድ ዓይነት ሥራ አልሠሩም፣ ነገር ግን ሁሉ ም ያገለግሉት የነበረው አንዱን ጌታ ነበር። ይህ ለቤተክርስቲያን ታላቅ ምሳሌ ነው። የእግዚአ ብሔር ሕዝብ እርስ በርሱ መወዳደር አቁሞ በታዛዥነት መተባበር ሲጀምር የመንግሥቱ ተህ ድሶ እንደሚያድግ ያሳያል።

**ተግባራዊ መግለጫ፡-** በግላችን ሙሉውን ቅጥር ላንጠግን እንችላለን፣ ነገር ግን በእኛ እጣ ክፍል ላይ ታማኝ ሆነን ከቀጠልን፣ የመንግሥቱን መታደስ እየረዳን ነው።

**ማጠቃለያ፡-**

የነህምያ መጸህፍ የመጀመሪያው ክፍል የሚያሳየን እውነት የእግዚአብሔር መንግስት መታደስ የሚጀምረው በሰው ፍላጎት ሳይሆን እግዚአብሔር ሸክምን በሰጣቸው ስወች መሆኑን እንዲሁም የመንግስቱ ተሀድሶ ስራ በእምነት ላይ የተመሰረተ ራዕይ እንደሚያስፈልገውና ይህ ራዕይ ድግሞ በአንድ ሰው ጥረት የሚፈጸም ሳይሆን የመንግስቱን ህዝቦች ሁሉ የሚያሳትፍ መሆኑን ነው።ስለዚህ እያንዳንዱ የመንግስቱ ዜጋ በመንግስቱ ተሀድሶ ውስጥ ጠቃሚና ተፍላጊ ሰው መሆኑን በመቀበል የሚሰራውን ድርሻ መውሰድና ከሌሎችጋር በመተባበር መንግስቱን ለማደስ መነሳታ አለበት።